# በጀርመን ሀገር ከሚገኙ የሶስቱ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ድጋፊ ሰጪ ድርጅቶች የተሰጠ የጋራ መግለጫ

25. Juni 2008

ከረዥም ጊዜያት ጀምሮ በሀገራችን የሚታየው የማህበራዊና የፖለቲካ ቀውስ ምንጩና መሰረቱ በአንድ ወገን በጉልበት የተያዘውን የመንግስት ስልጣን ላለመልቀቅ ሲባል ያለውን የመንግስት ሀይል ሁሉ በመጠቀምና በሌላው ወገን ደግሞ ድምፁ እንዲከበርለት በሚታገል ህዝብ መካከል የሚደረገው ትንንቅ ነው።

የግንቦት 7 1997 ዓ.ም. ምርጫም ከዚህ ተነጥሎ የሚታይ ክስተት አይደለም። በዚያ ወቅት የሀገራችን ህዝብ በኢትዮጵያችን ረዥም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘውን የምርጫ እድል በመጠቀም ፍፁም ሰላማዊ በሆነ መንገድ እኔን ይወክለኛል ጥቅሜንም ያስከብርልኛል ብሎ ላመነበት ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ (ለቅንጅት) እንዲያስተዳድረው ሀላፊነቱን ሰጥቶት ነበር።

አሁንም የግንቦት 1997 ውጤት የሚያሳየን አቢይ ነገር ቢኖር ህዝባችን በኢትዮጵያ ሀገራችን የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶችን ተከብረው ማየት እንዲሁም በህዝቦቿ እኩልነትና መፈቃቀር ላይ የተገነባ ጠንካራ የኢትዮጵያ አንድነት የማይሸጥ የማይለወጥ ፅኑ ፍላጎቱ እንደሆነ ነው። የኢህአዴግ ጭቆና፣ መብት ረገጣ፣ አፈናና ግድያ ሳይበግረው ዛሬም በተገኘው መንገድ ሁሉ የህዝብን ድምፅ፤ መብቱንና የሀገሩን ለኡዋላዊነት ለማስከበር የሚታገለው ወገናችን ሰላምና ዴሞክራሲ ለሀገሪቱና ለጎረቤት ሀገሮችም መረጋጋት ወሳኝ መሆኑን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ነው።

ውድ የአንድነት ፓርቲ የመስራች ጉባዔ አባላት

እናንተ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን (አንድነትን) ለመመስረት እንደምትሰባሰቡ ከሰማንበት ግዜ ጀምሮ ይሔን ታሪካዊ ቀን በናፍቆት ስንጠብቀው ነበር። አሁን ደግሞ ይህ እውን ሆኖ ማየት ብቻ ሳይሆን ህዝባችን የወደደውንና አምኖ የተቀበለውን፡ የሚታግልለትን፣ በሰላማዊ ትግል የሚያምነውን የቅንጅትን መርሆ አሁንም ለናንተም ዋናው መርኋችሁ መሆኑን ለህዝባችንም ሆነ ለኛ በተለያዩ የአለም ክፍላት ተበታትነን ለምንገኝ ኢትዮጵያውያን ማሳወቃችሁ ከፍተኛ የመንፈስ እርካታ ሰጥቶናል።

ውድ የአንድነት ፓርቲ የመስራች ጉባዔ አባላት

እኛ ትግሉ ገና እንዳላበቃ የምንረዳው። በትክክል መናገር ባንችልም ጉዞው ረዥምና አድካሚ ይሆናል፡ ብዙ መስዋዕትነትም ሊጠይቅ ይችላል ብለን እንገምታለን። እናንተ እስካሁን የተቋቋማችኋቸው ወከባዎች፣ የከፈላችኋቸው መስዋዕትነቶችና ያሳያችሁን የዕምነት ፅኑነት የተነሳችሁለትን አላማ እግቡ ለማድረስ ያላችሁን ቁርጠኛንት ያስገነዝበናል። እኛም በጀርመን ሀገር የምንኖር በቅንጅት የድጋፍ ድርጅት ስም የተቋቋምነው ደጋፊ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችሁ እስከዛሬ ድረስ ከጎናችሁ እንደቆምን ሁሉ ዛሬም ከጎናችሁ በመቆም በሀገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ትግል ላይ ከኛ የሚጠበቅብንን አስተውፅዖ ለማበርከትና ትግሉን ለማፋፋም ዝግጁነታችንን እናረጋግጥላችኋለን።

ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ ተጋድሎ ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኖራለች!

- በጀርመን ኖርድራይን-ቬስትፋለን የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ድጋፍ ኮሚቴ
- የኑርንበርግና አካባቢው የቅንጅት ድጋፍ ማህበር
- በሙኒክና አካባቢው የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ድጋፍ ግብረ ሀይል